# ዓለምለኽ ማሕበር ዴሞክራሲያዊያን ተጋሩ

## አለም አቀፍ የትግራይ ተወላጆች ዴሞክራሲያዊ ማህበር.

## International Tigrean Democratic Association

Itda2005@yahoo.com

### ከዓለም አቀፍ የትግራይ ተወላጆች ዴሞክራሲያዊ ማህበር የተሰጠ መግለጫ

### ገድሎ ከሳሽ

ቅንጅት የታጠቀ ሃይል ሳይኖረውና ጉልበት ሳይጠቀም በኢትዮጵያ ታሪክ ለመጀመሪያ ጊዜ በሰላማዊ መንገድ በሚልዮኖች በሚቆጠሩ ዜጎች ተመርጧል፡፡ በተለይ አዲስ አበባ የአለም አቀፍ ድርጅቶችና የተለያዩ አገሮች ተወካዮች ስለሚኖሩባት በቀጥታም በተዘዋዋሪም ብዙ ታዛቢዎች ያሏት ከተማ በመሆኗ፣ ህዝቡ ተነፃፃሪ ነፃነት ተሰምቶት ቅንጅትን ከ80% በላይ ድምፅ በመስጠት መርጧል፡፡ የአዲስ አበባ ህዝብ የብሄር/ብሄረ-ሰቦች አባሎች ያካተተ በመሆኑ ምርጫው የብዙ ኢትዮጵያውያን ፍላጎት የሚያንፀባርቅ ነው፡፡ ህዝቡ የተሰማው ተነፃፃሪ ነፃነት ግን ከኢህአዴግ ጥይት ሊያድነው እንዳልቻለ ከምርጫው በኋላ ተረጋግጠዋል፡፡ ስለዚህ ምርጫ 97 ባንድ በኩል ባገራችን ስልጣን በጉልበት የመያዝ ባህል ቀርቶ ህዝብ ተወካዮቹን በሰላም የመምረጥ መብቱ ቢረጋገጥ ህዝቡ ለሰላማዊ ለውጥ ብቃት እንዳለው አሳይተዋል፤ በሌላ በኩል ግን አገዛዙ የህዝብ ውሳኔ ለመቀበል ዝግጁ እንዳልሆነና የተወሰኑ ተቃዋሚ ድርጅቶችም ካገዛዙ መሳሪያነትና ከግል ጥቅማቸው ባሻገር የመሰረታዊ ለውጥ ራእይ እንደሌላቸው ምርጫው አረጋግጧል፡፡ ከዛም በላይ ምርጫው በሰው ህይወትና ነፃነት ላይ ከፍተኛ ጉዳት አስከትሎና ቅንጅትን አንድ በቀላሉ የማይፋቅ የሰላማዊ ትግል አርማ አድርጎ አልፏል፡፡

ለምርጫ 97 የፖለቲካ ድርጅቶች ውድድር በተደረገበት ጊዜ አቶ መለስ በተቃዋሚ ሃይሎች (በአቶ መለስ ኢንተርሃመዌ በተባሉት) ዘር የማጥፋት አደጋ የተጠነሰሰ አስመስለው ህዝብን ሲቀሰቅሱ በተለይ በማኸል አገር በሚኖር የተወሰነ የትግራይ ህዝብ ላይ ስጋት ፈጥሯል፡፡ በቅድሚያ ግጭቱ እንዲኖርና ፀጥታ በማስከበር አሳበው የለመዱትን ጭፍጨፋ ለማካሄድ የፈለጉት አቶ መለስ እንደሆኑ ግልፅ ነበር፡፡ አቶ መለስ በጥልቀት በማያውቋቸው የውጭ ሃይሎች "ዴሞክራሲያዊ" እንዲባሉ ይፈልጉ እንጂ ዴሞክራሲያዊ ሊሆኑ በፍፁም አይችሉም፡፡ ስለዚህ አገዛዙ ምርጫውን የጠላትና ወዳጅ መለያ አድርጎ ስላየው እንደ ጠላት የሚፈርጃቸውን ዜጎች ለማሳደድ ተጠቅሞበታል፤ የዴሞክራሲ ሂደቱንም አቋርጦታል፡፡

በፈጠራ የተወነጀሉት የቅንጅት መሪዎች አንዳንድ ግለ ሰቦች (የአቶ መለስም ሊሆኑ የሚችሉ) በተወሰኑ የትግራይ ተወላጆች ላይ የጥቃት እርምጃዎች ስለወሰዱ የአቶ መለስ የሰበብ ፍለጋ እቅድ እንዲሳካ አድርገዋል፡፡ ቅንጅት ግን እንደ ድርጅት በጋራ ውስኔ ደረጃ ያቀደውም የፈፀመውም ወንጀል የለም፡፡ ሆኖም ከቅንጅት መሪዎች ውስጥ በየግል አገዛዙ

ሊያወናብድበት በሚፈልገው ደረጃ ወንጀል ባይፈፅሙም ስህተቶች ሊፈፅሙ ወይም ስህተቶች እንደተፈፀሙ አውቀው ሳያርሙ ሊቀሩ ይችላሉ፡፡ ቅንጅት በውስጡ የሃሳብ ልዩነትም እየፈቀደ ተጠናክሮ ከራሱ ይሁን ከሌሎች በስሙ ህዝብን የሚያቃቅሩትን ግለሰቦች መግታት ይኖርበታል፡፡ ቅንጅት ባጭር የድርጅት እድሜውና ገና ድርጅታዊ መዋቅሩ ባልዘረጋበት ጊዜ ሁሉንም በስሜት የሚደገፉትን ዜጎች መቆጣጠር፣ ማስታገስና ማዘዝ የሚችልበት ሁኔታም አልነበረም፡፡ ግፋ ቢል ቅንጅት ማድረግ የሚችለው ደጋፊዎቹን መለመን ነበር፡፡ ይሁን እንጂ ባጭር ጊዜ ለብዙ ህዝብ ድምፁን ለማሰማት ሬድዮና ቴለቪዥንን ሳይጠቀም መልእክትን ማዳረስ የሚችልበት እድል አልነበረውም፡፡ ዶክተር ብርሃኑ ነጋ በመፅሃፋቸው በትግራይ ህዝብ ላይ ያነጣጠረ የጥላቻ ፅሁፍ ስለተሰራጨ፣ እሳቸው ባገርና በህዝብ ጉዳይ ላይ ከኢህአዴግ ጋር ልዩነት ሊኖር እንደማይገባ አምነው፣ ከኢህአዴግ ለአቶ ተክለወይኒ ስልክ ደውለው ፀረ ህዝብ የሆነውን ቅስቀሳ በመቃወም የጋራ መግለጫ ለማውጣት እንዲተባበሯቸው እንደጠየቁ፣ ይሁን እንጂ ከኢህአዴግ ትብብር እንዳለገኙ ገልፀዋል፡፡ በመንግስት ቁጥጥር ስር የሆኑ የመገናኛ ብዙሃንም የቅንጅትን ፅሁፍ እንዳላወጡ ዶ/ር ብርሃኑ ጠቅሰዋል፡፡

የቅንጅት መሪዎች በሰኔውና ጥቅምቱ ጭፍጨፋዎች ማኸል በምርጫው አካሄድና ውጤት ቅሬታቸውን ገልፀው፣ ህዝብ ድምፁን የማስከበር መብቱ እንዲጠቀም ቢገፋፉም በ299 ጣቢያዎች የተደረጉት ምርጫዎች እንዲጣሩ ያነሱትን ተቃውሞ ትተው፣ በማንም ዴሞክራሲያዊ ስርአት ተቀባይነት ያላቸውን የዴሞክራሲ ተቋሞች እንዲገነቡ እንደ ቅድመ-ሁኔታዎች (የሰራዊት፣ የፍርድ ቤት፣ የምርጫ ቦርድ ወዘተ ገለልተኝነት) እንዲሟሉ ጠይቀው ወደ ምክር ቤት እንደሚገቡ ገልፀው ነበር፡፡ አገዛዙ የመግባባትና የመቻቻል ባህል ቢኖረው፣ ለሰላም የሚቆም ቢሆንና ያገርንና የህዝብን መረጋጋት ቢያስቀድም ኖሮ እነዛ በቅንጅት የቀረቡ ቅድመ-ሁኔታዎች እንዳይሟሉ አፉን ሞልቶ በይፋ የሚቃወማቸው አይደሉም፡፡

ከምርጫ 97 እስካሁን ድረስ ባለው የአቶ መለስ የገድሎ ከሳሽ ተዋስኦ (ትያትር) የህሊና እስረኞቹና ደጋፊዎቻቸው ሲሰቃዩ ክሱ የተከሳሶቹ ሳይሆን የአስከሳሹ ወንጀልና የስርአቱ ወራዳነት የታሪክ ሰነድ ሆኗል፡፡ ለዚህ ትያትር ትእዛዞች የሚፈልቁት ካንድ ሰው ማለትም ከአቶ መለስ ብቻ ሆነው ኣላማቸው ቅንጅት በሰላማዊ መንገድና በህዝብ ፍላጎትም ቢሆን ስልጣን እንዳይዝ ወይም ጠንካራ ተቃዋሚ ሃይል እንዳይሆን መግታት ነው፡፡ በእነዚህ ትእዛዞች መሰረት ታጣቂዎች ያልታጠቁ ሰላማዊ ሰልፈኞችን ገድለዋል፤ አስገዳዮቹና ገዳዮቹ ግን አልተከሰሱም፡፡ አቃብያነ ህግ በሰላማዊ ዜጎች ላይ የውሸት ክሶች መስርተው በአንቀፆች የተደገፉ ግድያዎች ለማስፈፀም በህሊና እስረኞች ላይ የሞት ቅጣት እንዲፈፀም አመልከተው ነበር፤ ዳኞቹ ደግሞ በራሳቸው ሃሳብ የሚመሩና የሞት ቅጣትን ያልተቀበሉ መስለው እስረኞቹ እስኪሞቱ ድረስ እንዲታሰሩ ፈርደዋል፡፡

ትያትሩ ቀጥሎ የህሊና እስረኞቹ ነፃነታቸው ተነፍገው ኢያለና ደጋፊያቸው ህዝብ በጭፍጨፋዎች በተሸማቀቀበት፣ እስረኞቹ እንኳንና ለነፃነታቸው ለህይወታቸውም ዋስትና ባጡበት ሁኔታ ጥፋተኛነታቸውን እንዳመኑ እየተገለፀ ነው፡፡ ሁሉንም ወሳኙ አቶ መለስ መሆናቸው እየታወቀም ስለ ሽማግሌዎችና የይቅርታ ቦርድ ሚናዎች ይወራል፡፡ ለመሆኑ ሽማግሌዎች በደርግና በአቶ መለስ አገዛዝ ሚና አላቸው? ሽማግሌዎች በተሸምጋዮች ተሰሚነት የሚኖራቸው በተሸምጋዮቹ ላይ ጫና ማድረግ ሲችሉና እምቢተኛ ችላ የማይለው እርምጃም መውሰድ ሲችሉ ነው፡፡ ባገራችን በድሮ ጊዜ የሃይማኖት መሪዎች ባለ ስልጣኖችን በርግማንም አስፈራርተው ተቀባይነት ያገኙ ነበር፤ ባሁኑ ጊዜ ያሉት ባለስልጣኖች ግን ለሽማግሌዎች ደንታ የላቸውም፡፡ ለምሳሌ ያህል የኢትዮጵያና ኤርትራ መንግስቶችን ለማስታረቅ የሞከሩት ሽማግሌዎች (ከሽማግሌዎቹ አንዱ አሁንም እስረኞቹን እንዳነጋገሩ እየተገለፀ ነው) ምንም ውጤት ሊያመጡ አልቻሉም፡፡ እንዲያውም

ሽማግሌዎች ቅንነት እያላቸውም የባለስልጣኖች ትእዛዝ በመፈፀም ደካማው የተነገረውን እንዲቀበል ሊያግባቡ ይችላሉ፡፡ የቅንጅት ሰዎችም ባላጠፉበት እንዳጠፉ መገለፁ በምን ምክንያት እንደሆነ ለወደፊቱ መታወቁ አይቀርም፡፡ ሆኖም ቁም ነገሩ የእስረኞቹ መፈታት እንጂ አገዛዙ ለዛ የሚሰጠው ምክንያት አይደለም፡፡ሽማግሌዎቹ ላደረጉት ጥረት ምስጋና ይገባቸዋል፤ በባህላችን መሰረት ሽምግልና በአምባገነኖችም ደረጃ ተቀባይነት እንዲኖረው፣ ፍትሕም እንዲያካትትና የአምባገነኖች መሳሪያ ሆኖ ጉልበት የሌላቸው ዜጎች ሳያጠፉም ይቅርታ ለመጠየቅ የሚገደዱበት እንዳይሆን እንደ ተቋም በጣም ከፍተኛ ጥንካሬ ያስፈልገዋል፡፡

ስለዚህ አቶ መለስ በምርጫ ስልጣን እንዳይወስዱባቸው የፈሯቸውን ዜጎች አሳስረው፣ በውሸት አስከስሰው፣ አሰቃይተው፣ ወንጀለኛ አሰኝተው፣ በሞት ቅጣት አስፈራርተው፣ ከእስር ቤት ሳይወጡ እንዲሞቱ አስፈርደው፣ ጥፋት እንደፈፀሙ "አምነዋል" አሰኝተው የህሊና እስረኞቹን አስፈትተዋል፡፡ ቀጪው እስረኞቹን መፍታታቸው ለ19 ወሮች አሳስረው በማሰቀየታቸው የፈለጉትን አድርሰው ስለረኩም የኢትዮጵያውያን ትግልና የውጭ ሃይሎች ጫና እየበረታ እንደሚሄድ ስለተገነዘቡም ሊሆን ይችላል፡፡ ሆኖም አቶ መለስ ራሳቸው የፈፀሟቸውን የግድያ ወንጀሎች እስረኞችን በማስፈረም የእስረኞች ጥፋት አስመስለው ለማቅረብ ስልጣንንና ሽምግልናን በመጠቀም የሚያደርጉት ሽወዳ በወንጀል ከመጠየቅ እንደማያድናቸው ተገንዝበው በግልፅ ወንጀላቸውን አምነው ከህዝብ ይቅርታ ቢጠይቁ ይሻላል፡፡ አሁንም በሺዎች የሚቆጠሩ የታሰሩና በመታሰር ላይ ያሉ የፖለቲካና የህሊና እስረኞች አሉ፡፡ የታሰሩት ካለ ምንም ቅድመ ሁኔታ መፈታት አለባቸው፤ የማሰር ግፉም ይቁም፡፡

የህሊና እስረኞቹ ድሮውም ሊነፈጋቸው የማይገባውን ነፃነታቸው በማግኘታቸው የሚሰማንን ደስታ ለእነሱና ለቤተሰቦቻቸው እንገልፃለን፡፡ የቅንጅት መሪዎች የነሱ መታሰርን ተከትሎ በድርጅታቸው ውስጥ የተከሰተውን ትርምስ አስተካክለው በኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ስርአት እንዲመሰረት የጀመሩትን ሰላማዊ ትግል እንደሚቀጥሉና በህዝብ ውስጥ የቀሰቀሱትን የለውጥ ተስፋ እውን እንደሚያደርጉት ተስፋ እናደርጋለን፡፡

ዓለም አቀፍ የትግራይ ተወላጆች ዴሞክራሲያዊ ማህበር
ሐምሌ 1999 ዓ.ም